ቁጥር OFAGP-06.13/3/42
ቀን 10/09/2012

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለትምህርት ሚኒስቴር

አዲስ አበባ

ጉዳዩ ፣ የሚኒስቴሩን የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰው ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፣ 14 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ፣13 ገጽ አባሪ ፣ ገጽ የሂሳብ መግለጫዎች ና 1ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች የአተገባበር መርሀ ግብር ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን ።

ከሰላምታ ጋር

ወርቅአፈራሁ ወንድሙ
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የትምህርት ሚኒስቴር

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የትምህርት ሚኒስቴር የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል::

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆን በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት መ/ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ /የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፤
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፤
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፤
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፤
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፤
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፤

<u>**ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣**</u>

የሚኒስቴሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በውጪ አገር በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚማሩ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ድጋፍ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲፕሎማቲክ፤ ሚሲዮኖችና ዩኒቨርሲቲዎች የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገበት የባንክ ማስረጃ ቢኖርም ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ መሆናቸውን የሚገልጽ የሬጅስትራር ማስረጃና የሚማሩበት ትምህርት ቤት ገንዘቡ እንዲከፈለው የጠየቀበት ማስረጃ የሌለ ከመሆኑም በተጨማሪ የተላከው የኪስ ገንዘብ በትክክል ለተማሪዎች መድረሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ፣

- በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 44200 ብር 141,133,280.68 እና በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 40613 ብር 14,178,351.00 በድምሩ ብር 155,311,631.68 ተልኮ በተሰብሳቢ ተይዞ የነበረውና
- በቀን 17/04/2011 በክፍያ ማረጋገጫ ቁጥር 00043585 በድምሩ ብር 5,822,080.77 በደቡብ አፍሪካ ስር አ/አበባ ዩኒሳ ዩኒቨርስቲ ለሚማሩ ተማሪዎች የተከፈለው ክፍያ፤

በአጠቃላ ድምር ብር 161,133,712.45 ከላይ የተገለጹት ማስረጃዎች ሳይቀርቡ የተወራረደና በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣

2. በሴፕቴምበር 19/2018 እ.ኤ.አ ከአለም ባንክ በተፃፈ ኢሜል ትምህርት ሚኒስቴር የጠየቀው ስልጠና ሥልጠናው በአዲስ አበባ የሚሰጥ እና ኬኒያ ከሚሰጠው ጋር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ መሆኑንና በአዲስ አበባ ቢደረግ አዋጭ እንደሆነ ገልፆ ሳለ ብር 1,776,233.34 ለውሎ አበል ተከፍሎ ኬንያ እንዲሰለጥኑ የተደረገ መሆኑ፤
3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ Anhui telecommunications engineering co-ltd ከተባለ ድርጅት ጋር ለ300 ት/ቤቶችና ለ10 ዩኒቨርሲቲዎች ለሚያሰራው የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ዝርጋታ እና በዝርጋታው ሂደት ውስጥ የተካተቱ እንደ ስልጠና የመሳሰሉትን ሁኔታዎች ለማሰራት ውል የተዋዋለ ሲሆን፤
   - ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከድርጅቱ ጋር ውል ሲዋዋል ከ183 ቀን በላይ እንደሚሆን እየታወቀ ድርጅቱ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሳይኖረው (ከሚመለከተው መስሪያ ቤት ፍቃድ ሳያወጣ) ግገር ተፈጽሞ በመገኘቱ ሻጩ መክፈል የሚገባውን ብር 14,120,580.21 ከት/ም ሚኒስቴር የሂሳብ ቁጥር የተቀነሰ መሆኑ፤
4. በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደ ብር 33,473,352.79 የተሰብሳቢ ሂሣብ የሚገኝ መሆኑ፤
5. በሚ/ቤቱ በጊዜ ገደቡ ለሚመለከተው አካል ያልተከፈለ ብር 3,219,806.04 የሚገኝ መሆኑ፤

ከላይ በተገለፁት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የሚኒስቴሩ የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳይም፡፡

1. **ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤**

1.1 የመ/ቤቱ የሰው ሃብት የአስተዳደር የስራ ክፍል በቁጥር 23/1-9901/30/35 በቀን 13/09/2010ዓ.ም በበጀት ዓመቱ የለቀቁ ሰራተኞች ባቀረበው መረጃ መሰረት አቶ ጌታሁን ብሬ ተረፊ ከህዳር 18,2011 ዓ.ም ጀምሮ የለቀቁ ቢሆንም የህዳር ወር ሙሉ ደመወዝ በመከፈሉ አላግባብ ብር 933.46 በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱ፤

1.2 ከተለያዩ የሂሳብ መደቦች ከመደበኛ ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት ብር 81,241,447.28፤ ከ ካፒታል በጀት ብር 1,387,602,548.20፤ በጠቅላላ ድምር ብር 1,468,843,995.48 ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤

2. **ሌሎች ጉዳዮች**

ምንም እንኳን በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ባይኖራቸውም መሠረታዊና ጉልህ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥርና የአፈጻጸም ድክመቶች ቀጥለው ተመልክተዋል፡፡

**2.1 የአላቂ እና የቋሚ እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣**

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት በዩኒቨርስቲው ያለ አገልግሎት በተቀመጡ ቋሚ ንብረቶችና አላቂ ንብረቶች ላይ በመመሪያው መሠረት እርምጃ መውሰዱን እንዲሁም በንብረት ሂሳብ ላይ አግባብ ያለው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን እንዲሁም ለቋሚ ንብረቶች ተገቢው እንክብካቤና አካላዊ ጥበቃ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በአላቂ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የሚወገዱ እቃዎች ከአዲስ እቃዎች ጋር የተቀመጡ መሆኑ፤
- ከአንድ አመት በላይ የሆናቸው የሚወገዱ እቃዎች፤
- ብዛት ያላቸው የተለያዩ የመኪና ጎማዎች፣ቶነር 10ኤ ብዛት 8 ፣ቶነር 11 ኤ ብዛት 5፤
- ፓንቸር መካከለኛ በዛት 12 ፣ ሌክስመርክ 510/610 ብዛት 20 ፣ፎቶ ኮፒ ቶነር 2,318 ብዛት 4 እና እስቶክ ካርድ ብዛት 1000 እና የተለያዩ እቃዎች የተገኘ መሆኑ፤

**ከአንድ ዓመት በላይ የሆናቸው የሚወገዱ እቃዎች**

ብዛት ያላቸው የተለያዩ የመኪና ጎማዎች፣ ቶነር 10A ብዛት 8፣ ቶነር 11A ብዛት 5፣ ፓንቸር መካከለኛ ብዛት12፣ሌክሲ ማርክ 510/610 ብዛት 20፣ ፎቶ ኮፒ ቶነር ብዛት 4 እና እስቶክ ካርድ ብዛት 1,000 እና የተለያዩ እቃዎች የተገኘ መሆኑ፤

2.2 **በ2008፤ በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸውን ግኝቶች በተመለከተ፤**

**እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2008 በጀትዓመት**

- በውጪ አገር በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚማሩ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ድጋፍ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲፕሎማቲክ፤ ሚሲዮኖች እና የዩኒቨርሲቲዎች የባንክ ሂሳብ ገቢ ለተደረገበት የባንክ ማስረጃ ቢኖርም ተማሪዎች በትምህርት ላይ መሆናቸውንና የተላከው የኪስ ገንዘብ ለተማሪዎች መድረሱን የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ ማስረጃ ሳይቀርብ በድምሩ ብር 5,375,664.79 በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፤
- የገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ተ/ሽ/ቀ5/59 በቀን 29/10/2007 የትምህርት ሚኒስቴር ለ13 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ካፒታል በጀቱን እንዲያስተዳድርለት GIZ-IS ከተባለ ድርጅት ጋር በተደረገው ውል መሰረት በጀቱ በጥቅል ወደ ድርጅቱ እየተላለፈ ክፍያ እንዲፈጽም እንዲሁም የትምህርት ሚኒስቴር በስሙ ባሳተመው ደረሰኝ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ተቀናሽ እንዲያደርግ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲሰበስብ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን ገልጾ ድርጅቱ ከኮንትራክተሮች ላይ ሰብስቦ ገቢ ያላደረገውን የመንግስት ገንዘብ እንዲሁም በትም/ሚኒስቴር ስም የታተመውን በድርጅቱ ዘንድ የሚገኘውን ደረሰኝ በሙሉ በአስቸኳይ ተሰብስቦ ለኢ/ገ/ጉ/ባለስልጣን ተመላሽ እንዲያደርግ በገለጸው መሰረት አፈጻጸሙን ለማጣራት ገንዘቡ መሰብሰብ በሚገባው ልክ ለመሰብሰቡና የተሰበሰበው ገንዘብ ሁሉ በትክክል ለገቢዎችና ጉምሩክ ገቢ መሆኑን ለማረጋገጥ ቢሞከርም ሂሳቡን ለማጣራት የሚያስችል ሰነዶችንም ሆነ ስለ ሁኔታው በቂ ማብራሪያ ለማግኘት ባለመቻሉ ሂሳቡን ማጣራት አለመቻሉ፤

- በሰው ሃብት አስተዳደር በተሰጠን መረጃ መሰረት ከ01/02/2008 ጀምሮ በጡረታ ለተገለለ አንድ ሰራተኛ የጥቅምትና የህዳር ወር 2008 ዓ.ም ደመወዝ በድምር ብር 2,364.00 ያለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱ፤

## እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2009 በጀት ዓመት

- ከኮሌጆች ለተውጣጡ 15 ባለሙያዎች የተቋቋመ የጥናት ግብረ ሀይል የመጀመሪያው ዙር ለ20 ቀን በአራራት ሆቴል ጥናቱ ሲካሄድ፤ ከብሪቲሽ ካውንስል ከሚገኘው ድጋፍ የሚተካ በሚል ለውሎ አበልና ለሙያ አበል ብር 478,200.00 ክፍያው ከመደበኛ በጀት የተፈፀመ ሲሆን በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ ሲገባው ቀጥታ ወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ እና ለመደበኛ በጀት ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- መ/ቤቱ ለከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት የሚውል የተለያዩ የትምህርት መሳሪያዎችን ለመግዛት የሚያማክር የግዥ አማካሪ ለመቅጠር በ25/02/1998 በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በግልጽ ጨረታ ተወዳድሮ ያሸነፈው የግዥ አገልግሎት ድርጅት በቀን 14/01/1999 በብር 2,983,757.20 ለመስራት ውል ተፈራርሞ ስራውን ከጀመረ በኋላ የስራው 50% ክፍያ ተፈፅሞለት በ22/10/2003 ውሉ ተቋረጠ፡፡ ሆኖም ስራው 80% ስለደረሰ ቀሪው 30% ብር 963,577.48 ሊከፈለኝ ይገባል በማለት እንዲከፈለው በተደጋጋሚ በመጠየቁ፤ የመ/ቤቱ ሚኒስትር ዴኤታ በቀን 16/04/2007 በቁጥር 7/260/1349/07 ለድርጅቱ ቀሪውን ብር በጠየቀው መሰረት ክፍያ እንዲፈጸም የታዘዘ ከመሆኑ በተጨማሪ የመስሪያ ቤቱ የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በ22/03/2007 ለሚኒስትሩ ቢሮ ኃላፊ በተጻፈ ማስታወሻ የውሉን 80% ያጠናቀቀ ከሆነ ድርጅቱ የጠየቀው ቀሪ 30% ክፍያ እንዲከፈለው ቢደረግ የተሻለ መሆኑን ምክንያቱም ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ቢሄድ የማያዋጣ እና መ/ቤቱን ለተጨማሪ ወጪ እንዲዳርግ ከማድረጉ በተጨማሪ ከተቋሙ ጋር ያለውን የመልካም ስራ ግንኙነት እንዳያሻክር ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል አስተያየት የሰጠ ቢሆንም መ/ቤቱ ክፍያውን ሳይከፍል በመቅረቱ ድርጅቱ ክስ በመመስረቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 13/01/2009 በዋለው ችሎት ከተቋረጠበት 14/10/2003 ውሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ በጠቅላላው 5 ዓመት ከ7ወር ያልተከፈለውን ብር 963,577.48 እና 9% ህጋዊ ወለድ ብር 484,197.68 በድምር ብር 1,447,775.15 በፍርድ ቤቱ በመወሰኑ መ/ቤቱ አላግባብ

ብር 484,197.68 በክትትል እና የአሰራር ችግር ምክንያት ተጨማሪ ወጪ እንዲከፍል መደረጉ፤

- በውጪ አገር በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚማሩ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ድጋፍ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲፕሎማቲክ፤ ሚሲዮኖችና እና በዩኒቨርሲቲዎች የባንክ ሂሳብ ገቢ ለተደረገበት የባንክ ማስረጃ ቢኖርም ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ መሆናቸውንና የተላከው የኪስ ገንዘብ በትክክል ለተማሪዎች መድረሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ በድምር ብር 157,383,533.13 ክፍያ በመፈጸም በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፤

2010 <u>በጀት ዓመት</u>

- ካሳዎች ለሚመለከተው ግለሰብ መከፈሉል ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአጠቃላይ ድምር ብር 73,982,403.47 ወደ ግለሰቦቹ ሂሳብ ቁጥር ገብቶ ለግለሰቦቹ ሊከፈል ሲገባ ለዞኖች እና ወረዳዎች ገ/ኢ/ል/ ቢሮ እና ለዩኒቨርሲዎች አላግባብ የተከፈለ መሆኑ እና የሁሉም የመሬት የይዞታ ማረጋገጫ ያልቀረበ መሆኑ፤
- አቶ ታምራት አርጋታ ዋንስራ የቀድሞው የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ሹፌር ስለነበሩ ሚኒስትሩ ወደ ሌላ ቦታ ሲዛወሩ ሹፌሩንም ይዘው በመሄዳቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ ላይ ሳይሆኑ የመስከረምና ጥቅምት፤ ከታህሳስ-ሚያዚያ (7ወር) በሥራ ላይ ሳይሆኑ 12,463.5 ተከፍሏቸው መገኘቱ እና ከለቀቁ በኋላ የግንቦትና የሰኔ ወር ደመወዝ ብር 3,561.00 በድምሩ ብር 16,024.50 ተከፍሏቸው መገኘቱ፤
- ኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ ለሚያስተምሩ ሁለት ዓመት ያለፋቸው የህንድ መምህራን ታክስ የሚደረጉ መሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲከናወን ሁለት ዓመት ያለፋቸው መምህራን በበጀት ዓመቱ ብቻ ብር 313,879.62መቆረጥ የነበረበት የስራ ግብር ታክስ ያልተቆረጠ መሆኑ፤
- በውጪ አገር በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚማሩ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ድጋፍ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲፕሎማቲክ፤ ሚሲዮኖችና እና ዩኒቨርሲቲዎች የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገበት የባንክ ማስረጃ ቢኖርም ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ መሆናቸውን የሚገልጽ የሬጅስትራር ማስረጃና የሚማሩበት ትምህርት ቤት ገንዘቡ እንዲከፈለው የጠየቀበት ማስረጃ የሌለ እና ገንዘቡን ስለመቀበሉ ማስረጃ ያላቀረበ ከመሆኑም በተጨማሪ የተላከው የኪስ ገንዘብ በትክክል ለተማሪዎች መድረሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ በድምሩ ብር 250,845,261.90 የተከፈለ

ሲሆን ከዚህ ውስጥ የተላከላቸው የተማሪዎች ዝርዝር ሳይኖር ብር 31,124,988.45 ክፍያ ተከፍሎ የተገኘ ከመሆኑም በተጨማሪም ጉዳዩን እንዲያስፈፅሙ ለሚያደርጉ ደመወዝ እና የፅህፈት መሳሪያዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያቀርብ መሆኑ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0031720 በቀን 12/06/2010 በሂሳብ መደብ 2241105(6255) ከኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት የኮንቴይነር አገልግሎት ግዥ ብር 1,421,728.71 በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ/ Credit Note ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- በደረሰኝ ቁጥር 1880 ክፍያ ሲፈጸም የቀረበው ደረሰኝ በብር 127,703.26 የሚያንስ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ ብቻ በኦዲት ናሙና በታየው ለሲ እና ኢ ወንድማማቾች የብረት ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ብር 15,835,398.73፤ ስቲሊ አር ኤም አይ ሃ /የተ/የግ/ኩ ብር 243,168.01፤ ናሽናል ሲሚንቶ አ.ማ ብር 9,561,510.02፤ ሙገር ሲሚንቶ አ.ማ ብር 1,190,280.00፤ ደርባ ሲሚንቶ አ.ማ ብር 26,300,508.29 በድምሩ ብር 53,130,865.05 ክፍያ ሲፈጸም፡-
    - ለሥራ ተቋራጮች የብረትና ሲሚንቶ ቅድሚያ የተሰጠ ቢሆንም መከታተያ ሌጀር የሌለ በመሆኑ የትኛው ህንጻ ሥራ ተቋራጭ ላይ ምን ያህል አወራርዶ ቀሪው ስንት እንደሆነ የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ እና በሂሳብ ምዝገባ ላይም የማይታይ መሆኑ፤
    - የግንባታ ግብዓቶች ግዥ ሲፈጸም የፍላጎት መጠየቂያን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ለምሳሌ ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ላይ ብረት የሚያስፈልገው ባለ 16,18,20 ሆኖ ሳለ የተላከላቸው 13,000 ቤርጋ ባለ 10 ብረት ሲሆን 3,000 ቤርጋ በበጀት ዓመቱ የተላከ መሆኑ፤

- ከግንባታዎች ጋር ተያይዞ በዲዛይን የሥራ ተለዋጭ ስራ /varation order/ ብር 17,575,661.60እና ተጨማሪ ሥራ /supplementary agreement/ ብር 1,054,182.89 በሚል በድምሩ ብር 18,629,844.49 ለኮንትራክተሮች ክፍያ እንደተፈጸመ ቢገልፅም የሥራውን ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ በተጨማሪም የሥራውን አስፈላጊነት የአማካሪ ድርጅቱ ያቀረበው ሠነድ፣ የፕሮጅክት ጽ/ቤት ኃላፊ ያረጋገጠበትና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር ያሳውቀበት ደብዳቤ እና የሥራ

አመራሩ የወሰነበት ቃለ ጉባዔ ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረቡ ትክክለኝነቱንለማረጋገጥ ያለመቻሉ፤

- አዳቡልቱም ዩኒቨርሲቲ የውል ጊዜው የተጠናቀቀ ቢሆንም ስራው ያላለቀ በመሆኑ ጊዚያዊ ርክክብ ያልተደረገበት መሆኑ፤
- የመጨረሻ ርክክብ  ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ላይ መደረግ ቢኖርበትም ያልተደረገ መሆኑ፤

ዶ/ር ትእፌራሁ ወንድሙ
የከፍተኛ ትምህርት ጥራት ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

**የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**